# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 226490

ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ሰናይት አድነው

ደጀኔ አያንሳ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፀሐይ ለሚ የሕፃን ኮኬት ምናስ አሳዳጊ፡- ቀርቧል

ተጠሪዎች ፡-

1. ኤልያስ ወንድዬ
2. ትዕግስት ወንድዬ
3. ሰላማዊት ወንድዬ
4. ፍቅርተ ወንድዬ

ጠበቃ ካሣሁን አውራሪስ ቀርቧል

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 881 ሥር የተመለከተውን መስፈርት የማያሟላ ፤ ኑዛዜው የተደረገው የባልና ሚስት በሆነ ንብረት ላይ ሆኖእያለ ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት የሥር ፍርድ ቤቶች የሟች የወ/ሮ ጽጌ እሼተን ንብረት በሚመለከት በሥር ያልተነሳን የይርጋ መቃወሚያን መሠረት በማድረግ ኑዛዜ የተደረገበት ንብረት ያረፈበትን ይዞታ ስፋት እና አዋሳኞቹን የማያመለክት ለአፈፃፀም ምቹ ያልሆነ ፤ እንዲሁም በዝምታ ወራሾችን ከውርስ

የነቀለን ኑዛዜ አይፈርስ መባሉ ፤ እንዲሁም ሕፃን ኮኬት የሟች አቶ ምናስ ወንድዬ ልጅ እና ወራሽ መሆኗ በመዝገብ ቁጥር 11050 ላይ የተሰጠ የፀና ውሳኔ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕፃኗ ልጅነት ተጣርቶ ይወሰን ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ጉዳዩ በሰበር እና በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ወጪና ኪሳራ እንዲወንላቸው አመልካች ግንቦት 5 ቀን 2014 ዓ/ም የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቀርቧል፡፡

ክርክሩ የውርስ ድርሻ ጥያቄን የሚመከለት ሆኖ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን በተመለከተው የሰበታ ወረዳ ከተማ ፍርድ ቤት አመልካች በከሳሽነት ተጠሪዎች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- የተጠሪዎች ወንድም ከሆነው ሟች አቶ ምናሴ ወንድዬ ጋር በነበራቸው ግንኙነት በ2000 ዓ/ም ኮኬት ምናሴ የሚትባል ልጅ ማፍራታቸውን ፤ አቶ ምናሴ ወንድዬ በ2011 ዓ/ም መሞታቸውን ፤ እንዲሁም እናት እና አባቱ እንደቅደምተከተላቸው በ1992 ዓ/ም እና 2011 ዓ/ም መሞታቸውን በመግለጽ ፤ ሕፃን ኮኬት ምናሴ አባቷን ተክታ የወንድ አያቷ አቶ ወንድዬ ደምሴ እና የሴት አያቷ ወ/ሮ ጽጌ እሸቴን የመውረስ መብት ሲላላት በሟች አያቶቿ የተፈራ በተጠሪዎች እጅ ያለው በሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 07 ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተመለከተው 120 ሉክ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት ፤ 30 ሉክ ሶስት ክፍል ቆርቆር ቤት እንዲሁም 39 ቆርቆር ሶስት ክፍል ሰርቭ ቤት በ446 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈ ግምቱ 5,000,000.00 (አምስት ሚሊዮን) ብር የሆነ መኖሪያ ቤት ድርሻዋ እንዲወሰንላት ጠይቃለች፡፡ ተጠሪዎች በመልሳቸው፡- ወ/ሮ ፀሐይ ለሚ ከአቶ ምናስ ወንድዬ ጋር በሕግ የታወቀ ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ሕፃኗ የሟች ወንድማቸው ልጅ ስላልሆነች የዘረ - መል (D.N.A) ምርመራ እንዲደረግ እንዲሁም ሟች አባታቸው የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ የውርስ ሃብቱን ያከፋፈሉ በመሆኑ አመልካች የመውረስ መብት አላት የሚባል ከሆነም ማግኘት የሚትችለው በኑዛዜው መሠረት የሟች አባቷን ድርሻ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የሰበታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ለክርክሩ እልባት መስጠት ያስችለኛል ያላቸውን ጭብጮች ይዞ መዝገቡን እንደመረመረው ሕፃን ኮኬት ወንድዬ የሟች ምናስ ወንድዬ ልጅ መሆኗ በመዝገብ ቁጥር 11050 የተሰጠ የፀና ውሳኔ በማስረጃነት ቀርቦ እያለ የውርስ ድርሻዋን ለማግኘት ባቀረበችው ክስ ላይ የሟች ምናሰ ወንድዬ ልጅ አይደለችም በማለት በተጠሪዎች የቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ ያደረጉት ኑዛዜ የሟች ባለቤታቸው ወ/ሮ ጽጌ እሸቴን ድርሻ ስለሚጨምር እና ኑዛዜ የተደረገበት ንብረት አዋሳኝ እና ስፋቱን የማያመለክት ግልጽነት የጎደለው ለአፈፃፀም የሚያስቸግር በመሆኑ ፈራሽ ነው፡፡ ወራሾች ሰባት መሆናቸው ስለተረጋገጠ የአመልካች 1/7ኛ ድርሻዋ እንዲሰጣት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን ተጠሪዎች ባቀረቡት ይግባኝ የተመለከተው በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሕፃን ኮኬት የሟች ምናስ ወንድዬ ልጅ እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ለመሆኗ የፀና ውሳኔ ያለ በመሆኑ ተጠሪዎች ሕፃኗ የሟች ልጅ አይደለችም የሚሉ ከሆነ ውሳኔውን ማሸር ሲገባቸው ሕፃን ኮኬት ምናስ የሟች ምናስ ወንድዬ ልጅ አይደለችም በማለት ያቀረቡት ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፡፡ ኑዛዜው የሟች ወ/ሮ ፅጌ እሸቴን ድርሻ አካቷል ለተባለውም አቶ ምናስ ወንድዬ የእናቱን ድርሻ በተመለከተ ያቀረበው ጥያቄ በሌለበት እና አቶ ወንድዬ ደምሴ የሟች ወ/ሮ ፅጌ እሸቴ የንብረት ድርሻን ለ19 ዓመታት በእጁ አድርጎ በኑዛዜ ለወራሾቹ ሲያስተላልፍ ያቀረበው ተቃውሞ ሳይኖር አመልካች በዚህ አግባብ ባቀረበችው መቃወሚያ ኑዛዜው መፍረሱ አግባብነት የለውም፡፡ ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ትልቁን ቤት እና ሰርቪስ ቤቶቹን ማን መውረስ እንዳለበት እንዲሁም የወራሾቹን ድርሻ የሚያመለክት ሆኖእያለ ግልጽነት የጎደለው እና ለአፈፃፀም የሚያስቸግር ነው መባሉ ኑዛዜውን ለመሻር በቂ ምክንያት ስላልሆነ ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ መሠረት የሟች አቶ ምናስ ወንድዬን ድርሻ ልጁ ሕፃን ኮኬት ምናስ ሊትወርስ ይገባል በማለት የሰበታ ከተማ ወረዳ ከተማ ፍርድ ቤት ውሳኔን አሻሽሏል፡፡

አመልካች የውርስ ድርሻ ክፍፍሉ ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ መሠረት መደጉን በመቃወም የይግባኝ አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሲያቀርቡ ፤ ተጠሪዎችም አመልካች የሐሰት ማስረጃ በማቅረብ የወሰደችውን የወራሽነት ማስረጃ መቃወሚ የሚትችሉት የወራሽነት ማስረጃውን የተሰጠበትን መዝገብ ላይ ተቃውሞ በማቅረብ ነው መባሉ አግባብ አይደለም በማለት የመስቀለኛ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በቀረበው የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ መዝገቡን እንደመረመረው ፤ ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 881 እና 882 ድንጋጌ ሥር የተመለከቱ መስፈርቶችን የሚያሟላ ፤ ሟቹ ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጅንስ ቀርቦ ፈቃዱን የገለፀበት ፤ የግል ንብረቱን የሆነውን ትልቁን ቤት ለወራሾቹ እኩል ያካፈለበትና ከዚህ ቤት ውጭ ያለው ቤት የእሱ አመሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ ኑዛዜው ሊፈፀም አይችልም የሚለው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሟች ምናስ ወንድዬ ሟቹ አባቱ አቶ ወንድዬ ደምሴ የሟች እናቱ ወ/ሮ ፅጌ እሸቴን ድርሻ ጨምሮ ኑዛዜ ሲያደርግ ያቀረበው ተቃውሞ ሳይኖር አመልካች የቀረበው ተቃውሞ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ሊፈርስ የሚችልበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ ኑዛዜው ሊፀና ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 842 መሰረት የወሰደችው ወራሽነት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 45587 ላይ በሰጠው እስገዳጅ ውሳኔ እንደማስረጃ የሚወሰድ እንጅ እንደመጨረሻ ውሳኔ ስለማይታይ አመልካች የሟች ምናስ ወንድዬ ልጅ መሆኗ ሳይጣራ አባቷን ተክታ

የተጠሪዎችን እናትና አባት ለመውረስ ትችላለች ተብሎ መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ አመልካች ከሟች ምናስ ወንድዬ የተወለደች መሆን / አለመሆኑ ተጣርቶ ውሳኔ እንዲያገኝ መዝገቡን በመመሪያ መልሶታል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለቱ አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎቱ፡- የሥር የወረዳ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ሕፃን ኮኬት ምናስ የሟች አቶ ምናስ ወንድዬ ልጅ መሆኗ አስቀድሞ በመዝገብ ቁጥር 1105 ውሳኔ ስላገኘ ልጅነቷን ተቀብሎ የውርስ ንብረቱን እንዲተካፈል ወስኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ልጅነቷ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ሥር ፍርድ ቤት የመለሰበት አግባብ ፤ እንዲሁም አመልካች የሟች ልጅ ነች ከተባለ ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ መሠረት ሊትወርስ ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪዎች ተከታዩን መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ ያደረጉት ኑዛዜ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ሁለት ምስክሮች ፊት የተደረገ በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟላ ፤ የወራሾች ድርሻ የሚለይ በመሆኑ እና ንብረቱ ያረፈበት ይዞታ አለመገለጹም ኑዛዜውን ተፈፃሚ እንዳይሆን ስለማያግደው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊነቀፍ የማይገባ መሆኑን ፤ ከ20 ዓመት በኋላ የቀረበው የሟች ወ/ሮ ፅጌ እሸቱ የውርስ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ፤ ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ኑዛዜ እድርጓል ቢባል እንኳን ምክንያቱ ኑዛዜን ለመሻር የማያበቃ መሆኑን ፤ በመዝገብ ቁጥር 1105 ላይ የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃ እንጅ ጣልቃ ገብቶ መከራከር ወይንም መቃወሚ የማይቀርብበት ሆኖእያለ አመልካች ወራሽነቷን አረጋግጣለች በማለት ተጠሪዎች የሟች ልጅ አይደለችም በማለት ያቀረቡትን መቃወሚያ ማሰረጃ ሳይሰማ እና ሳይመረመር ውሳኔ መሰጠቱ የግራቀኙን እኩል የመሰማት መብት የምነፍግ በመሆኑ ጉዳዩ ተጣርቶ ውሳኔ እንዲያገኝ የተሰጠው ውሳኔ አግባብ በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ሐምሌ 27 ቀን 2014 ዓ/ም የተፃፈ ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ቅሬታው ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ሟች አበቷን ተክታ የሟች አያቶቿን ለመውርስ አቤቱታ ያቀረበችው በመዝገብ ቁጥር 11050 ላይ የሟች አባቷ ወራሽ ናት ተብሎ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 842 መሠረት ከሰበታ ወረዳ ከተማ ፍርድ ቤት ጥቅምት 11 ቀን 2012 ዓ/ም የተሰጣት ማስረጃ መሠረት አድርጓ ሲሆን ፤

ማስረጃው የተሰጠው ወ/ሮ ፀሐይ ለሚ ከሟች አቶ ምናስ ወንድዬ ጋር በነረበራቸው የፍቅር ግንኙት የተወለደችው ሕፃን ኮኬት አባት ሟቹ አቶ ምናስ ወንድዬ በመሆኑ የሕፃኗ የሟች ወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ባቀረቡት አቤቱታ በአቤቱታ አቅራብዋ የተቆጠሩት የአንድ ወገን ማስረጃ ቃል መሠረት አደርጎ የተሰጠ ነው፡፡ ተጠሪዎች በአመልካች የቀረበው የውርስ ድርሻ ይገባኛል ጥያቄ ወ/ሮ ፀሐይ ለሚ ከአቶ ምናስ ወንድዬ ጋር በሕግ የታወቀ ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ሕፃኗ የሟች ወንድማቸው ልጅ ስላልሆነች የዘረ - መል (D.N.A) ምርመራ ተደርጎ ልጅ መሆኗ ሳይጣራ የሟች ልጅ እና ወራሽ መባሏን ተቃውሟል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የሰበታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሕፃን ኮኬት ወንድዬ የሟች ምናስ ወንድዬ ልጅ መሆኗ በመዝገብ ቁጥር 11050 የተሰጠ የፀና ውሳኔ ባለበት የውርስ ድርሻዋን ለማግኘት በቀረበ ክርክር ላይ ልጅ ናት ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ መቃወም አይቻልም በማለት በተጠሪዎች የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃ ሳይሰማ ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉንና ይግባኝ ሰሚው በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከዚህ አንፃር የሰበታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናቱን ከመዝገቡ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጅ ወራሽነቷን በማረጋገጥ ለአመልካች የተሰጠው የወራሽነት ማስረጃ በአመልካች ብቻ የቀረበውን የአንድ ወገን ማስረጃ በመቀበል የሚሰጥ ማስረጃ (Declaratory judgment) ለመክሰስ መብትና ጥቅም ያለው መሆኑን አሳይቶ የድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ለማቅረብ በማስረጃነት የሚቀርብ ፣ በማንኛውም ተዓማኒነት እና ክብደት ባለው ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል ማስረጃ በመሆኑ ማስረጃው በተሰጠበት መዝገብ ላይ መብት ወይንም ጥቅሜን ይነካል በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት የፍርድ መቃወሚያ የሚቀርብበት አለመሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 82679 እና በሌሎችም በርካታ መዛግብት ላይ አስገዳጅ ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካች የሟች የአቶ ምናስ ወንድዬ ልጅ መሆን አለመሆን በፍርድ ተረጋግጦ ውሳኔ እንዲያገኝ ወደ ሥር ፍርድ ቤት መመለሱ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 142(3) እና 160 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ከዚህ አፃር የቀረበው የሰበር ቅሬታ የሕግ ድጋፍ ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ሊፀና አይገባል የሚሉበትን ምክንያቶችን በመዘርዘር ኑዛዜው እንዲፈርስ ያቀረቡትን አቤቱታ ተጠሪዎች ኑዛዜው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሟች የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 881 እና 882 ድንጋጌ ሥር የተመለከቱ መስፈርቶችን የሚያሟላ ፣ ሟች ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንስ ቀርቦ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፈቃዱን የገለፀበት ፤ የግል ንብረቱ የሆነውን ትልቁን ቤት ለወራሾቹ እኩል ያካፈለበትና ከዚህ ቤት ውጭ ያሉት ቤቶች የእሱ አመሆኑን የገለፀበት በመሆኑ ኑዛዜው ሊፈፀም አይችልም የሚለው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም በማለት አጽንቷል። በእርግጥ ኑዛዜውን በተመለከተ በግራ ቀኙ መካከል ያለው ክርክር ስለተጠናቀቀ ዳግም በጉዳዩ ላይ ክርክር እንድደረግ መፍቀድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ዓላማ የሚፃረር ቢሆንም ፤ የአመልካች የሟች ልጅነት(ወራሽነት)ተጣርቶ ኑዛዜውን ለማሻር አቤቱታ ለማቅረብ በፍሥ/ሥሕ/ቁ 33(2) መሠረት መብት እና ጥቅም ያላት መሆን / አለመሆኑ ሳይጣራ ኑዛዜው መፍረስ አለበት/የለበትም በሚል ጭብጥ ላይ ክርክር ተደርጎ ኑዛዜውን ማጽናት ሥነ ሥርዓቱን የተከተለ ባለመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል።

**ውሳኔ**

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪው ችሎት ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 345169 የካቲት 24 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት በመዝገብ ቁጥር 393907 መጋቢት 9 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ተሻሽሏል*** ።
2. የሕፃን ኮኬት ምናስ የሟች አቶ ምናስ ወንድዬ ልጅነት ተጣርቶ ውሳኔ እንዲያገኝ በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ***አልተነካም (ፀንቷል)።***
3. ሟች አቶ ወንድዬ ደምሴ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ሊሻር አይገባም በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል።
4. አመልካች ሟቹን አቶ ወንድዬ ደምሴን የመውረስ መብት ያላት መሆኑ/አለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ኑዛዜውን በመቃወም ባቀረበችው የክስ አቤቱታ መነሻነት ኑዛዜው መፍረስ አለበት ወይስ የለበትም በሚለው ጭብጥ ላይ ክርክር ተደርጎ ኑዛዜው ሊፈርስ አይገባም መባሉ ስህተት ነው።
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረስ ብለናል።
6. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ።

***መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።***

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

-

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም